# የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ
# ድጋፍ ኮሚቴ - ቦስተን

**955 Mass. Ave. P.O.Box 341**
**Cambridge, MA 02139**
**E-mail: cudboston@yahoo.com**


**Date: Aug.11, 2006**
**Ref. N°·04/002/2006**

## ለ፡ ኢትዮ-ሚዲያ ድህረ-ገጽ አዘጋጆች

# የሕዝብ አጋርነት በተግባር ሲገለጽ

በተለያዩ ጊዜያትና ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብን ወደ ተሻለ ህይወት ለማምጣት እንታገላለን በሚል የትግል መድረክ የተለያዩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ተፈጥረዋል።

ነገር ግን ግማሾቹ መንገዳቸውን ሳይጨርሱ በመሀል ሲቀሩ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ የሀገራቸውን ጉዳይ ወደኋላ በማለት የራሳቸውን ጥቅም በማስቀደም ወደተነሱበት ዓላማና ግብ ሳይደርሱ ቀርተዋል።

ሌሎች ደግሞ ጭራሽ መነሻቸውን ረስተው የራሳቸውን ዕምነትና የአመራር የበላይነት በማስቀደም ሕዝቦችን አሳልፈው ለአደጋ በማጋለጥ በህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዲደርስና እንዲሁም ንፁህን የኢትዮጵያ ልጆች ወደ እስር እንዲገቡ ያደረጉ ግለሰቦችና ቡድኖች አሉ። እነዚህንና የመሳሰሉትን ዕውነታዎች በዓለም ላይ ላሉ ኢትዮጵያውያን ለማሳወቅ የኢትዮ-ሚዲያ ድህረ-ገጽ ያደረገው አስተዋጽዎ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። በተለይ በሀገራችን ላይ ለተንሰራፋው አምባገነን መንግስት የራስ ምታት ነው።

የኢትዮ-ሚዲያ ድህረ-ገጽ የሚያስተላልፈው ሚዛናዊና ትክክለኛ መረጃ ሁላችንም ዕውነታውን እንድንረዳ ያደረገ ሲሆን ወደፊትም በዚሁ ድንቅ ሥራችሁ እንደምትቀጥሉበት እምነታችን ነው። በዚህ አጋጣሚ ለ5ኛው ዓመት በዓላችሁ እንኳን አደረሳችሁ እያልን ለቀጣይ ሥራችሁ መልካም ምኞታችንን እየገለጽን ይህንን ድንቅና ታሪካዊ በዓል ላዘጋጁትና ላስተባበሩት ሁሉ ምስጋናችንንና አድናቆታችንን በቦስተንን አካባቢው የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ድጋፍ ሰጪ ድርጅት ዓባላትና ደጋፊዎች ስም እናቀርባለን።

**የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ**
**ድጋፍ ሰጪ ድርጅት**
**ቦስተን**